# የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር
# የደረቅ ቆሻሻ አስተዳደር ኤጀንሲ

## የደረቅ ቆሻሻ መልሶ መጠቀምና ኡደት ማህበራት አደረጃጀትና የአሰራር መመሪያ ቁጥር 22/2013



# 1.መግቢያ

በከተማችን አዲስ አበባ የሚመነጨውን ደረቅ ቆሻሻ በአግባቡ በመለየት ለመልሶ መጠቀምና ኡደት አገልግሎት እንዲውል የማድረግ መልካም ጅማሬዎች ሲኖሩ ለማሳያነትም የሀይላንድና የወረቀት ደረቅ ቆሻሻዎችን በተሻለ ሁኔታ የገበያ ትስስር በመፍጠር የጽዳት ማህበራት እየለዩ ለመልሶ መጠቀምና ኡደት አገልግሎት የማዋል ተግባር እየተከናዎነ ይገኛል፡፡

ነገር ግን በከተማው ከሚመነጨው ደረቅ ቆሻሻ አብዛኛውን ለመልሶ መጠቀምና ኡደት አገልግሎት ማዋል የሚቻል ቢሆንም አሁንም በከተማው የሚመነጨው ደረቅ ቆሻሻ በሚፈለገው ደረጃ እየተለየ ለመልሶ መጠቀምና ኡደት አገልግሎት ማዋል ባለመቻሉ አብዛኛው ደረቅ ቆሻሻ ወደ ማስወገጃ ቦታ እየተጓጓዘ እንዲወገድ እየተደረገ ይገኛል፡፡ በተለይ በከተማው በርካታ መጠን ያለው ስብርባሪ ጠርሙስ፣ መስታዎትና የብርጭቆ፣ አሮጌ ማዳበሪያ ቀረጢት፣ አዶጌ ወረቀትና ካርቶን፣ ጀሪካን ቁርጥራጭ፣ ውድቅዳቂ ብረታ ብረት፣ አሮጌ የኤሌክትሮኒክስ እቃዎች ወዘተ በአግባቡ ተለይቶ ለመልሶ መጠቀምና ኡደት አገልግሎት እየዋሉ አይገኙም፡፡

እነዚህን ከላይ የተዘረዘሩትን ደረቅ ቆሻሻዎች በአግባቡ በመለየትና በመሰብሰብ ለመልሶ መጠቀምና ኡደት አገልግሎት እንዲውሉ በማድረግ በዘርፉ ለበርካታ ዜጎች የስራ እድል መፍጠር የሚያስችል ሲሆን በተጨማሪም ደረቅ ቆሻሻን ወደ ሀብትነት በመለወጥ ለሀገር የሚያበረክተውን ሀገራዊ ፋይዳ ማሳደግ ይቻላል፡፡ ስለዚህ ደረቅ ቆሻሻን በስፋት ለመልሶ መጠቀምና ኡደት አገልግሎት ለማዋል ያስችል ዘንድ በመልሶ መጠቀምና ኡደት ዘርፍ ብቻ የሚሰማሩ አዳዲስ ማህበራትን አደራጅቶ በዘርፉ ለማስገባት የሚያስችል ይህ የመልሶ መጠቀምና ኡደት የማህበራት አደረጃጀትና የአሰራር መመሪያ ተዘጋጅቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## <u>ጠቅላላ ድንጋጌ</u>

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ **"የደረቅ ቆሻሻ መልሶ መጠቀምና ኡደት ማህበራት አደረጃጀትና የአሰራር መመሪያ ቁጥር ፳፪/፪ሺ፲፫"** ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### ፪. ዓላማ፤

ይህ መመሪያ ለመልሶ መጠቀምና ኡደት አገልግሎት የሚውሉ (ስብርባሪ ጠርሙስና ብርጭቆ፣ አሮጌ የማዳበሪያ ቀረጢት፣ ቁርጥራጭ ብረታ ብረት፣ አሮጌ ጀሪካን፣ አሮጌ ወረቀትና ካርቶን፣ ጨርቃ ጨርቅ ወዘተ) ደረቅ ቆሻሻዎችን በአግባቡ በመሰብሰብ ለመልሶ መጠቀምና ኡደት አገልግሎት እንዲውል በማድረግ ለዜጎች የስራ እድል ለመፍጠርና ደረቅ ቆሻሻን ወደ ሀብትነት መለወጥ ነው፡፡

### ፫. የቃላት ትርጓሜ

የቃላት አገባብ ሌላ ትርጉም ካልተሰጣቸው በቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

፩. ***"ከተማ"*** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ ነው፡፡

፪. ***"ኤጀንሲ"*** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ የደረቅ ቆሻሻ አስተዳደር ኤጀንሲ ነው፡፡

፫. ***"ደረቅ ቆሻሻ"*** ማለት ጥቅም የማይሰጥ ወይም የማይፈለግ ተብሎ የሚጣል ጠጣር ወይም ከፊል ጠጣር የሆነ ቁስ ሆኖ ለሌላው ሰው ግን ጥቅም ሊሰጥ ይችላል፡፡

፬. ***"የመልሶ መጠቀምና ኡደት ማህበር"*** ማለት የተለያዩ ለመልሶ መጠቀምና ኡደት አገልግሎት የሚውሉ ደረቅ ቆሻሻዎችን ከተለያዩ የህብረት ሽርክና ጽዳት ማህበራት፣ ከግለሰቦች፣ ከተቋማት፣ ከግንባታ ቦታዎችና ህገ-ወጥ የቆሻሻ መጣያ ቦታዎች በግዥ ወይንም በነጻ እየሰበሰበ ለእራሳቸው መልሰው ጥቅም ላይ የሚያውሉ ወይም መልሰው ጥቅም ለሚያውሉ ድርጅቶች የሚያቀርብ ነው፡፡

፭. ***"ህገወጥ ቆሻሻ መጣያ ቦታ"*** ማለት ህብረተሰቡ ቆሻሻን ለማከማቸት ከተፈቀደለት ቦታ ውጪ የሚጥልባቸው የወንዝ ዳርቻ፣ የተለያዩ ክፍት ቦታዎች፣ የግለሰቦችና የተቋማት አጥር ጥግ ወዘተ ማለት ነው፡፡

፮. ***"የመልሶ መጠቀም"*** ማለት ከደረቅ ቆሻሻ ውስጥ ጠቃሚ ዕቃዎችን በማውጣት በቀጥታ ወይም የተወሰነ ለውጥ አድርጎ ለተመሳሳይ ወይም ለተለየ አገልግሎት መጠቀም ማለት ነው፡፡

፯. ***"ኡደት ማድረግ"*** ማለት ከደረቅ ቆሻሻ ውስጥ ጠቃሚ ዕቃዎችን በማውጣት እንደገና በጥሬ ዕቃነት ወደ ፋብሪካ በማስገባት ከመጀመሪያው ዕቃ ጋር የሚመሳሰል ወይም የማይመሳሰል ጠቃሚ ዕቃ ማምረት ነው፡፡

**፬. መመሪያውን ማውጣት ያስፈለገበት ምክንያት**

በአዲስ አበባ ከተማ ከሚመነጨው ደረቅ ቆሻሻ ውስጥ አብዛኛው ፐርሰንት የሚሆነው ለመልሶ መጠቀምና ኡደት አገልግሎት በማዋል ወደ ሀብትነት መለወጥ የሚቻል ቢሆንም እስከ አሁን ባለው ሁኔታ ግን ግብዓቱ በተደራጀ መንገድ ተሰብስቦ ለመልሶ መጠቀምና ኡደት አገልግሎት የማይውል በመሆኑ አብዛኛው ደረቅ ቆሻሻ ወደ ማስወገጃ ቦታ እየተጓጓዘ እንዲወገድ እየተደረገ በመሆኑ በከተማው የደረቅ ቆሻሻ አወጋገድ ስርዓት ላይ ከፍተኛ ጫና ሲፈጥር ቆይቷል፡፡

ስለዚህ ይህንን ደረቅ ቆሻሻ (ስብርባሪ ጠርሙስና ብርጭቆ፣ አሮጌ ማዳበሪያ ቀረጢት፣ የኤሌክትሮኒክስ ውድቅዳቂዎች፣ አሮጌ ጨርቃ ጨርቅ፣ ብረታ ብረት፣ ፕላስቲኮችና ወረቀቶች፣ ብስባሽ ቆሻሻዎችን ወዘተ) በተደራጀ መንገድ በመሰብሰብና በመለየት ወደ ሀብትነት ለመለወጥና የከተማውን ጽዳት ለማሻሻል ብሎም ለዜጎች የስራ እድል ለመፍጠር እንዲቻል ይህ የአሰራር መመሪያ ተዘጋጅቷል፡፡

**፭. የመመሪያው ወሰን**

የዚህ መመሪያ ወሰን በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ስብርባሪ ጠርሙስና ብርጭቆ፣ አሮጌ የማዳበሪያ ቀረጢት፣ አሮጌ ወረቀትና ካርቶን፣ ቁርጥራጭ ብረታ ብረት፣ አሮጌ ኤሌክትሮኒክስ፣ የተለያዩ ጨርቃ ጨርቆች፣ ለኮምፖስት የሚሆን ብስባሽ ቆሻሻ፣ የእንስሳት አጥንት፣ የፕላስቲክ ጠርሙስ፣ ጀሪካን፣ ፌስታል፣ በመሰብሰብ በራሳቸው መልሰው ጥቅም ላይ ማዋል ወይም በዘርፉ ለተደራጁ ድርጅቶች በማቅረብ ላይ በተሰማሩ ማህበራት ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

# ክፍል ሁለት

## ፮. የየደረቅ ቆሻሻ መልሶ መጠቀም ማህበራት አደረጃጀት

፩. የደረቅ ቆሻሻ መልሶ መጠቀምና ኡደት ማህበራት በከተማው ከዚህ በፊት የቤት ለቤት ደረቅ ቆሻሻ ለመሰብሰብ ከተደራጁ የህብረት ሽርክና የጽዳት ማህበራት በአሰራራቸው የተለዩ ናቸው፡፡

፪. በዚህ አንቀጽ ቁጥር ፩ በተገለፀው መሰረት የደረቅ ቆሻሻ መልሶ መጠቀምና ኡደት ማህበራት ለመልሶ መጠቀምና ኡደት አገልግሎት የሚውል ደረቅ ቆሻሻ በጽዳት የሽርክና ማህበራት ወይም በግል የጽዳት ድርጅቶች ያልተያዙ ቦታዎች በመለየት ለመልሰው መጠቀምና ኡደት አገልግሎት የሚያውሉ ደረቅ ቆሻሻዎችን ብቻ የሚሰበስቡ ማህበራት ናቸው፡፡

፫. የደረቅ ቆሻሻ መልሶ መጠቀምና ኡደት ማህበራት እንደ ክፍለ ከተማው ነባራዊ ሁኔታና እንደ ግብዓቱ መጠን ታይቶ በሁሉም ወረዳ ወይም በተወሰኑ ወረዳዎች በማዕከል መደራጀት አለባቸው፡፡

፬. የደረቅ ቆሻሻ መልሶ መጠቀምና ኡደት ማህበራት ከደረቅ ቆሻሻ ኮምፖስት ለማምረት፤ ከደረቅ ቆሻሻ የተለያዩ ጌጣጌጦችን ለማምረት፤ የመልሶ መጠቀም የሚውሉ ደረቅ ቆሻሻ ሰብስቦ ለመሸጥ ወይም በራሳቸው ለማምረት ሲሉ መደራጀት ይችላሉ፡፡

## ፯. የደረቅ ቆሻሻ መልሶ መጠቀም ማህበራት የአሰራር ሁኔታ

፩. የደረቅ ቆሻሻ ለመልሶ መጠቀምና ኡደት ማህበራት ለመልሶ መጠቀምና ኡደት አገልግሎት የሚውሉ ደረቅ ቆሻሻዎችን በመግዛት ወይም ከተለያዩ ቦታዎች በመሰብሰብ ለራሳቸው መልሰው ጥቅም ላይ ማዋል ወይም ለመልሶ መጠቀምና ኡደት አገልግሎት ለሚያውሉ ድርጅት ማቅረብ ይችላሉ፡፡

፪. በዚህ አንቀጽ ቁጥር ፩ በተገለጸው መሰረት ለመልሶ መጠቀምና ኡደት የሚውሉ ደረቅ ቆሻሻ የሚሰበስቡ ማህበራት ከተለያዩ ድርጅቶች በግዥ ወይም በነጻ፤ ከህብረት ሽርክና የጽዳት ማህበራት በግዥ፤ ከግንባታ ቦታዎች በግዥ ወይም

በነጻ፣ ህገወጥ ቆሻሻ መጣያ ቦታዎችና ልዩ ልዩ ባህላዊና ሀገር አቀፍ ዝግጅት በሚደረግባቸው ቦታዎች ላይ ተጥለው የሚገኙትን መልቀም ወይም መሰብሰብ ይችላሉ፡፡

፫. ማንኛውም በደረቅ ቆሻሻ መልሶ መጠቀምና ኡደት የተደራጀ ማህበር መሰብሰብና ማከማቸት የሚችለው ለመልሶ መጠቀምና ኡደት አገልግሎት የሚውሉትን ደረቅ ቆሻሻ ብቻ ሲሆን ነገረ ግን ምንም ዓይነት ደረቅ ቆሻሻ ሰብስቦ ወደ ማስወገጃ ቦታ የማጓጓዝና የማስወገድ ተግባር ላይ መሳተፍ አይችልም፡፡

፬. ማንኛውም በደረቅ ቆሻሻ መልሶ መጠቀምና ኡደት የተደራጀ ማህበር በየዓመቱ የወረዳው ደረቅ ቆሻሻ አስተዳደር ጽ/ቤት በሚያዘጋጀው ውል መሰረት ከጽ/ቤቱ ጋር መዋዋልና መስራት ይገባዋል፡፡

፭. ማንኛውም በደረቅ ቆሻሻ መልሶ መጠቀምና ኡደት የተደራጀ ማህበር በዚህ ዘርፍ ተደራጅቶ መስራት የሚችለው ለአምስት ዓመት ብቻ ሲሆን ከአምስት ዓመት በኋላ ለመሸጋገር እንዲያመቸው ቢያንስ ከገቢው 20 ፐርሰንት መቆጠብ ይገባዋል፡፡

## ፰. የደረቅ ቆሻሻ መልሶ መጠቀም ማህበራት የማከማቻ ቦታና የስራ ግብዓት

፩. የደረቅ ቆሻሻ መልሶ መጠቀምና ኡደት ማህበራት ለሚሰበስቡት ግብዓት ማከማቻና የመስሪያ ቦታ በተመለከተ ማህበሩ በራሱ ወይም የወረዳው የደረቅ ቆሻሻ አስተዳደር ጽ/ቤት እና የሚያደራጃቸው ጥቃቅንና አነስተኛ በትብብር ያመቻቻሉ፡፡

፪. ማንኛውም የመልሶ መጠቀምና ኡደት ማህበር ለስራ አስፈላጊ የሆነውን የስራ ግብዓት በራሳቸው ወጪ አሟልተው መግባት አለባቸው፡፡

፫. የደረቅ ቆሻሻ መልሶ መጠቀምና ኡደት ማህበራት የሰበሰቡት ግብዓት ወደ ፋብሪካ ለመውሰድም ይሁን ወደ ሌላ ቦታ ሲያጓጉዙ በራሳቸው ተሽከርካሪ ወይም ግብዓቱን ከሚገዛቸው ድርጅት ጋር በሚያደርጉት የውል ስምምነት መሆን አለበት፡፡

፬. የደረቅ ቆሻሻ መልሶ መጠቀምና ኡደት ማህበራት የሰበሰቡት የመልሶ መጠቀምና ኡደት ደረቅ ቆሻሻ የአካባቢውን ገጽታን በማያበላሽ መልኩና የህብረተሰብ ቅሬታ እንዳያስነሳ ከመሬት በታች፣ እንደ እሮቶ ባለ እቃ ውስጥ፣ በአግባቡ ተጨፍልቆ

ወይም በማዳበሪያ ውስጥ ማከማቸት ይገባል፡፡ ግብዓቶችን በመሬት ላይ በትኖ ማስቀመጥ የተከለከለ ነው፡፡

**፱. የደረቅ ቆሻሻ መልሶ መጠቀም ማህበራት የክፍያ ዋጋ ሁኔታ**

፩. የደረቅ ቆሻሻ መልሶ መጠቀምና ኡደት ማህበራት የገቢ ሁኔታ ለመልሶ መጠቀምና ኡደት ሰብስበው በሚሸጡት ወይም አምርተው በሸጡት የመልሶ መጠቀምና ኡደት ምርት መጠን ይሆናል፡፡

፪. የደረቅ ቆሻሻ መልሶ መጠቀምና ኡደት ማህበራት የግብዓት ወይም የምርት ዋጋ ሁኔታ ግብዓቱን ወይንም ምርቱን ከሚረከባቸው ድርጅት ወይም ግለሰብ ጋር በሚያደርጉት የነጻ የገበያ ስርዓት መሰረት የዋጋ ድርድር በጋራ አድርገው የሚወሰን ይሆናል፡፡

፫. መንግስት ለህብረት ሽርክና የጽዳት ማህበራት ፌስታልና ፕላስቲክ ጠርሙስ ሰብስበው ሲሸጡ የሚሰጠውን ድጎማ ለመልሶ መጠቀምና ኡደት ለተሰማሩ ማህበራትም አይሰጥም (ምንም አይነት ድጎማ አይሰጥም)፡፡

፬. የህብረት ሽርክና የጽዳት ማህበራት ፌስታልና ፕላስቲክ ጠርሙስ ሰብስበው ሲሸጡ መንግስት የሚሰጠው ድጎማ እስኪቆም ድረስ በመልሶ መጠቀምና ኡደት የተሰማሩ ማህበራት ድጎማውን ሊያካክስላቸው በሚችል መልኩ የህብረት ሽርክና የጽዳት ማህበራት ከሚሸጡበት ዋጋ ላይ ተጨማሪ ዋጋ ከድርጅቱ በመደራደር ይሸጣሉ፡፡

**፲. የደረቅ ቆሻሻ መልሶ መጠቀም ማህበራት የማህበራት የስራ ክልል**

፩. የደረቅ ቆሻሻ መልሶ መጠቀም ማህበራት ለመልሶ መጠቀምና ኡደት አገልግሎት የሚውሉ ደረቅ ቆሻሻዎችን መሰብሰብ የሚችሉት ከተለያዩ ድርጅቶች በግዥ ወይም በነጻ፤ ከህብረት ሽርክና ጽዳት ማህበራት በግዥ፤ ከግንባታ ቦታዎች ድርጅቱን በማስፈቀድ፤ ከህገ-ወጥ ቆሻሻ መጣያ ቦታዎች፤ ሀገር አቀፍና ሃይማኖታዊ ዝግጅቶች በሚከናወንባቸው ቦታዎች በመልቀም ወይም በማስለቀም ይሆናል፡፡

፪. በዚህ አንቀጽ ቁጥር ፩ የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ የደረቅ ቆሻሻ መልሶ መጠቀም ማህበራት ከቤት ለቤት ምንም አይነት ቆሻሻዎችን መሰብሰብ አይችሉም፡፡ ነገር

ግን ኮምፖስት የሚያመርት ማህበር ከሆነ ለኮምፖስት የሚሆን ቆሻሻ ብቻ በወረዳው ፍቃድ ከመኖሪያ ቤት፣ ከተቋማት ወይም ከአትክልት ገበያ ማዕከላት እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡

፫. የደረቅ ቆሻሻ መልሶ መጠቀም ማህበራት በመመሪያው እንዳይሰበስቡ ከተከለከሉበት ቦታዎች ውጪ ከሌላ ወረዳም ቢሆን በመመሪያው መሰረት መሰብሰብ ወይም ግብዓቱን መግዛት ይችላሉ፡፡

፬. ለኮምፖስት ለሚሆን ደረቅ ቆሻሻ ኤጀንሲው ከግል ጽዳት ድርጅቶችና ከሌሎችም ጋር በመነጋገር ኮምፖስት ለሚሰሩ ማህበራት እንዲቀርብላቸው የሚደረግ ሲሆን የማህበራትን ቆሻሻ ከቤት ለቤት መውሰድ ግን የተከለከለ ነው፡፡

## ፲፩. ኢ-መደበኛ የመልሶ መጠቀም ደረቅ ቆሻሻ ክምችትን ስለመከላከል

፩. ማንኛውም አካል ከወረዳው እውቅና ውጪና ህጋዊ ፈቃድ ሳይኖረው በመንገድ ዳርና አካፋይ ወይም ባልተፈቀደ ቦታ ለመልሶ መጠቀምና ኡደት አገልግሎት የሚውሉ ደረቅ ቆሻሻ ማከማቸት የተከለከለ ነው፡፡

፪. የመልሶ መጠቀምና ኡደት የሚውል ደረቅ ቆሻሻ ያለወረዳው ህጋዊ ፈቃድ በወረዳው ውስጥ መሰብሰብም፣ መግዛት ሆነ ማከማቸት የተከለከለ ነው፡፡

፫. ከወረዳው እውቅና ውጪ ለመልሶ መጠቀምና ኡደት አገልግሎት የሚውሉ ግብዓቶችን በኢ-መደበኛነት የሚሰበስብ ድርጅት ወይም ግለሰብ በህጋዊ መንገድ ተደራጅቶ ወይም ፈቃድ አውጥተው መስራት ይገባቸዋል፡፡

## ፲፪. የደህንነት መጠበቂያ ግብዓት ስለማሟላትና መረጃ ስለመስጠት

፩. የደረቅ ቆሻሻ መልሶ መጠቀም ማህበራት የደህንነት መጠበቂያ ግብዓትና ቱታ በራሳቸው ወጪ ገዝተው የመልበስ ግዴታ አለባቸው፡፡

፪. የደረቅ ቆሻሻ መልሶ መጠቀም ማህበራት ቱታ ውሃ ሰማያዊ መሆን ይገባዋል፡፡

፫. ማንኛውም በመልሶ መጠቀምና ኡደት የተሰማራ ድርጅት/ግለሰብ አስፈላጊውን የመልሶ መጠቀምና ኡደት መረጃ የመስጠት ግዴታ አለበት፡፡

፬. ማንኛውም በመልሶ መጠቀምና ኡደት የተሰማራ ድርጅት/ግለሰብ ስለሸጠው ወይም መልሶ ጥቅም ላይ ስላዋለው የቆሻሻ መጠን ለመልሶ መጠቀምና ኡደት የዋለ መረጃው ለከተማው የደረቅ ቆሻሻ አስተዳደር ስርዓት መሻሻል ያለውን ፋይዳ ከፍተኛ በመሆኑ ሪፖርት በየወሩ ለወረዳው የማቅረብ ግዴታ አለበት፡፡

## ፲፫. ተጠያቂነት

፩. ማንኛውም በመልሶ መጠቀምና ኡደት የተሰማራ ድርጅት/ግለሰብ/ማህበር ግብዓቱን እዲሰበስብ ከተፈቀደለት ቦታ ውጪ ሲሰበስብ ወይም ሲያሰበስብ ከተገኘ ለመጀመሪያ ጊዜ የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ ይሰጠውና ለሁለተኛ ጊዜ ከደገመ ማህበሩ ከወረዳው ጋር የተዋዋለው ያለምንም ቅድመ ሁኔታ እንዲሰረዝ ይደረጋል፡፡

፪. ማንኛውም በመልሶ መጠቀምና ኡደት የተሰማራ ድርጅት/ግለሰብ/ማህበር የሚመለከተው አካል መረጃ ሲጠይቀው ትክክለኛ መረጃ የመስጠት ግዴታ አለበት፡፡ ይህን ካላደረገ ለሶስት ጊዜ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶት ካልታረመ ከወረዳው ጋር የተዋዋለው ውል ያለምንም ቅድመ ሁኔታ እንዲሰረዝ ይደረጋል፡፡

## ፲፬. የተለያዩ አካላት ተግባርና ኃላፊነት

### i. የደረቅ ቆሻሻ አስተዳደር ኤጀንሲ

፩. ለተደራጁ ማህበራት ገበያ ማፈላለግ

፪. ለማህበራቱ የአቅም ግንባታ ስልጠና መስጠት

፫. የአሰራር መመሪያና ስታንዳርድ ማዘጋጀት

፬. ክትትልና ድጋፍ ማድረግ

### ii. የክፍለ ከተማ ደረቅ ቆሻሻ አስተዳደር ጽ/ቤት ተግባርና ኃላፊነት

፩. በተመረጡ ወረዳዎች የደረቅ ቆሻሻ መልሶ መጠቀም ማህበራት እንዲደራጁ ማድረግ

፪. ለማህበራቱ ስልጠና መስጠትና የገበያ ትስስር መፍጠር

፫. በቋሚነት ክትትልና ድጋፍ ማድረግ

፬. ስራውን በቋሚነት መገምገምና ለችግሮች አፋጣን ምላሽ መስጠት

iii. **የወረዳ ደረቅ ቆሻሻ አስተዳደር ጽ/ቤት ተግባርና ኃላፊነት**

፩. የደረቅ ቆሻሻ መልሶ መጠቀም ማህበራት እንዲደራጁ ለጥቃቅንና አነስተኛ ጥያቄ ማቅረብና ሲደራጁ ወደ ስራ ማስገባት

፪. ለማህበራቱ ቋሚ ክትትልና ድጋፍ ማድረግና አካባቢው እንዳይበከል መቆጣጠር

፫. ማህበራቱ የሚያጋጥማቸውን ችግር በቅርበት መፍታትና ህጋዊ ውል በማዘጋጀት ከማህበራቱ ጋር መዋዋል፡፡

፬. ማህበራቱን ከሪሳይክሊንግ ድርጅት ጋር ውል እንዲዋዋሉ ያደርጋል፡፡

፭. በማህበራቱ ለተለዩ ቆሻሻዎች የገበያ ትስስር ይፈጥራል፡፡

፮. ወርሃዊ ሪፖርቶችን በመቀመር ለኤጀንሲው መላክ

፯. ወረዳው ለተደራጁ ማህበራት የማከማቻና የመስሪያ ቦታ ከጥቃቅንና አነስተኛ ጽ/ቤትና ከማህበሩ ጋር በመሆን ያመቻቻል፡፡

iv. **የደረቅ ቆሻሻ መልሶ መጠቀምና ኡደት ማህበራት ተግባርና ኃላፊነት**

፩. ማንኛውም የደረቅ ቆሻሻ መልሶ መጠቀም ማህበር ግብዓቱን ከተለያዩ ድርጅቶች፣ ከህብረት ሽርክና ጽዳት ማህበራት በግዥ፣ ከግንባታ ቦታዎች ድርጅቱን በማስፈቀድ፣ ከህገ-ወጥ ቆሻሻ መጣያ ቦታዎች በመልቀም ወይም በማስለቀም የሚሰበሰብ ይሆናል፡፡

፪. ማንኛውም የደረቅ ቆሻሻ መልሶ መጠቀም ማህበር የተሰበሰበውን ግብዓት አካባቢንና ማህበረሰቡን በሚጎዳ መልኩ፣ መተላለፊያ መንገድ መዝጋት፣ የግለሰቦችን አጥርና ንብረት በሚጎዳ መልኩ…ወዘተ ማከማቸት የለባቸውም፡፡

፫. ማንኛውም የደረቅ ቆሻሻ መልሶ መጠቀም ማህበር የቤት ለቤት ደረቅ ቆሻሻ መሰብሰብም ሆነ ማሰባሰብ ስራ ላይ መሳተፍ አይችልም፡፡

፬. ማንኛው የመልሶ መጠቀምና ኡደት አገልግሎት የሚውሉ ደረቅ ቆሻሻዎችን የሚያቀርብ ማህበር ወይም ድርጅት በዱቤ ላስረከበው እቃ ለሚያጋጥመው ችግር ማህበሩ በራሱ በውሉ መሰረት መፍታት (መጠየቅ) ይገባዋል፡፡ ለዚህም ችግር የትኛውም የመንግስት መስሪያ ቤት ተጠያቂ አይሆንም፡፡

፭. ተረካቢው ድርጅት ለጽዳት ማህበራቱ ለንብረቱ ማጠራቀሚያ ፎዴ ወይም ማዳበሪያ፣ የተለያየ ማሽን ከሰጠ ማህበሩ በአግባቡ የመያዝ ግዴታ አለበት፡፡ ነገር ግን ድርጅቱ የሰጠውን ማከማቻ ማህበሩ ከቀደደ፣ ካበላሸ፣ ከጣለ ወይም ለሌላ አካል አሳልፎ ከሰጠ ግምቱን የመክፈል ወይም ተመሳሳዩን የመተካት ግዴታ አለበት፡፡

፮. ማንኛው የመልሶ መጠቀምና ኡደት አገልግሎት የሚውሉ ደረቅ ቆሻሻዎችን የሚያቀርብ ማህበር ንብረቱን ከሚረከባቸው ድርጅት ጋር ንብረቱ የሚነሳበትን ቋሚ ፕሮግራም በጋራ በመወሰን በፕሮግራሙ መሰረት ውል የገባው ድርጅት እንዲያነሳላቸው የማድረግ ግዴታ አለባቸው፡፡

፯. ማህበራት ለመልሶ መጠቀምና ኡደት አገልግሎት ደረቅ ቆሻሻን ሲለዩ የደህንነት መጠበቂያ ግብዓቶችን የመጠቀም ግዴታ አለባቸው፡፡

፰. አካባቢን በሚበክል ሁኔታ ተዝረክርኮ ለተቀመጠ ለመልሶ መጠቀምና ኡደት አገልግሎት የሚውል ደረቅ ቆሻሻ ችግሩን የፈጠረው ማህበር በደረቅ ቆሻሻ አስተዳደር ደንብ መሰረት ተጠያቂ ይሆናል፡፡

፱. ፌስታልና የወረቀት ደረቅ ቆሻሻዎች በንፋስ በቀላሉ የሚበተኑ በመሆናቸው በአግባቡ ክዳን ባለው፣ በታሰረ እቃ ውስጥ ወይም ከመሬት በታች መከማቸት አለባቸው፡፡

v. **ለመልሶ መጠቀምና ኡደት አገልግሎት የሚውሉ ደረቅ ቆሻሻ የሚረከቡ ድርጅቶች ተግባርና ኃላፊነት**

፩. ለመልሶ መጠቀምና ኡደት አገልግሎት የሚውሉ ደረቅ ቆሻሻዎችን የሚረከብ ድርጅት ንብረቱን ከሚያቀርቡለት ማህበራት ጋር በቀጥታ ህጋዊ ውል በመግባት ብቻ ይሰራል፡፡

፪. ለመልሶ መጠቀምና ኡደት አገልግሎት የሚውሉ ደረቅ ቆሻሻዎችን የሚረከብ ድርጅት ንብረቱን ከማህበራት የሚረከብብትን ፕሮግራም በውሉ ላይ የማሳወቅ ግዴታ አለበት፡፡

፫. ደረቅ ቆሻሻ መልሶ መጠቀምና ኡደት አገልግሎት ላይ የተሰማራ ድርጅት የደረቅ ቆሻሻ ኤጀንሲ በሚያወጣው የአሰራር ስታንዳርድ፣ ደንቦችና መመሪዎች መሰረት የመስራት ግዴታ ይኖርበታል፡፡

፬. ደረቅ ቆሻሻ መልሶ መጠቀምና ኡደት አገልግሎት ላይ የተሰማራ ድርጅት ንብረቱን ለሚያቀርቡለት ማህበራት ወይም ድርጅት ወቅታዊ የገበያ ሁኔታ በሚፈቅደው አግባብ በውላቸው መሰረት የዋጋ ማስተካካያ ማድረግ ይገባዋል፡፡

፭. በደረቅ ቆሻሻ መልሶ መጠቀምና ኡደት አገልግሎት ላይ የተሰማራ ድርጅት በየወሩ ለመልሶ መጠቀምና ኡደት አገልግሎት ያዋለውን የደረቅ ቆሻሻ መጠን ለወረዳው ሪፖርት ማድረግ ይገባዋል፡፡

## ፲፭. የተጠያቂነት ስርዓት

❖ ማንኛውም አካል በዚህ መመሪያ የተሰጠውን ተግባርና ኃላፊነት ካልፈጸመ በህግ ተጠያቂ ይሆናል፡፡

## ፲፮. መመሪያውን ስለማሻሻል

❖ ይህ መመሪያ እንደ አስፈላጊነቱ በኤጀንሲው ሊሻሻል ይችላል፡፡

## ፲፯. መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ

❖ ይህ መመሪያ ከዛሬ 13/05/2012 ዓ፣ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የደረቅ ቆሻሻ አስተዳደር ኤጀንሲ**